የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ
NATIONAL ELECTION BOARD OF ETHIOPIA

ቁጥር አ1162/11/801

ቀን ታኅሣሥ 5 ቀን 2015 ዓ.ም.

ለደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል

ፖሊስ ኮሚሽን

ሀዋሣ፣

ጉዳዩ፣ የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ) በ19/03/2015 በቁጥር ኢዜማ/0146/15 እና በ20/03/2015 በቁጥር ኢዜማ/0199/15 በተፃፈ ደብዳቤ ለቦርዱ ያቀረበውን አቤቱታ ይመለከታል፤

የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ) በ19/03/2015 ዓ.ም. በቁጥር ኢዜማ/0146/15 በተፃፈ ደብዳቤ በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ጉራጌ ዞን እዣ ወረዳ ኢዜማን ወክለው በ2013 ዓ.ም. በተካሄደው ሀገር አቀፍ ምርጫ አሸንፈው የክልል ምክር ቤት አባል የሆኑት በአቶ ታረቀኝ ደግፌ ሕዳር 17 ቀን 2015 ዓ.ም. አዲስ አበባ ከሚገኘው መኖሪያ ቤታቸው በመንግስት የጸጥታ ኃይሎች ተይዘው ወዳልታወቀ ቦታ ተወስደዋል የሚል አቤቱታ እና በ20/03/2015 ዓ.ም. በቁጥር ኢዜማ/0199/15 በተፃፈ ደብዳቤ አቶ ታረቀኝ ደግፌ በተያዙበት ወቅት አካላዊ ጉዳት ስለደረሰባቸው የህክምና እርዳታ የሚያገኙበት መንገድ እንዲመቻች በመጠየቅ ለቦርዱ አቤቱታ አቅርቧል።

እንደሚታወቀው የኢትዮጵያ የምርጫ፤ የፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባና የምርጫ ሥነምግባር አዋጁ 1162/2011 መሰረት ቦርዱ የተጣለበት ሃላፊነት የፖለቲካ ፓርቲዎችን ማስተዳደር፤ በአመራርና በአባላቱ ላይ የሚደርስ ማናቸውም ጉዳይ መከታተል ነው። በዚህ መሰረት ኮሚሽኑ ለቦርዱ የቀረበው ጉዳይ ላይ ተገቢው ማብራሪያ እስከ ህዳር 30 ቀን 2015 ዓ.ም እንዲሰጥ ጠይቋል። ይሁንና ይህ ደብዳቤ እስከተጻፈበት ቀን ድረስ ኮሚሽኑ ለቦርዱ ጥያቄ የሰጠው ምላሽ የለም። በመሆኑም ይህንን ደብዳቤ ለሶስተኛ ጊዜ ቦርዱ ለመጻፍ ተገዷል።

ለድምጽዎ የሚያምኑን


አድራሻ - ቦሌ ክፍለ ከተማ
ሬስቶራንት ገባ ብሎ በስተቀኝ
አዲስ አበባ ኢትዮጵያ

ስልክ
+251 115 153468

ፋክስ
+251 115 510025

ፌስቡክ
/national-electoal-board-of-ethiopia-nebe

ትዊተር
@NEBEthiopia

ኢሜይል
contact@nebe.org.et

ድረ-ገጽ
www.nebe.org.et

በመሆኑም ምርጫ አዋጁ አንቀጽ 161 ማንኛውም ሰው አዋጁን በስራ ላይ ለማዋል በሚያስችል ሁኔታ የመተባበር ግዴታ ይጥላል። ስለዚህ ኮሚሽኑ ይህንን የህግ ግዴታ በመረዳት ከላይ በኮሚሽኑ ላይ በኢዜማ ፓርቲ የቀረቡትን አቤቱታዎች በተመለከተ አጣርቶ ምላሽ ያልሰጠበትን ምክንያት እንዲገልጽ እንዲሁም በጉዳዩ ላይ የደረሰበትን ሂደት በአስቸኳይ እንዲያሳውቅ በጥብቅ ቦርዱ ያሳውቃል።

ከበጎ ምኞት ጋር

ብርቱካን ሚደቅሳ
የኢትዮጵያ ብሔራዊ
ምርጫ ቦርድ ሰብሳቢ

*<u>ግልባጭ</u>፣*

- *ለኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ ፓርቲ (ኢዜማ)*

*<u>አዲስ አበባ</u>፣*